# Learning by Ear 2013

## "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ "መዘዙን መቀበል"

## EPISODE 14: እራስን መሆን

**AUTHOR: James Muhando**
**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**
**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ምህረት AND ቅዱስ IN TANDIKA**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ምህረት (F, 16)**

**SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት TALKS TO PRINCIPAL ሰብለ**

- **ወ/ሮ ሉሊት** (F, 40)
- **ጥበቃ (M, 60)**
- **ሰብለ (F, 50)**

**SCENE 3: በለጠ AND ዳንኤል FIGHT OVER BLANKET**

- **በለጠ (M, 16)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

## INTRO

### 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" "መዘዙን መቀበል" በሚል ርዕስ የሚቀርበውን ተከታታይ የሬዲዮ ድራማችን ለመከታተል በመታደማችሁ ደስ ብሎናል። ። ቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው የሚማሩ አፍሪቃውያን አዳጊ ወጣቶችን ታሪክ እስካሁን እየተከታተልን ነበር፡፡ ባለፈዉ ጊዜ ርዕሰ መምህርት ሰብለ ከተማሪዎቹ መካከል ንጉሴ አደንዛዥ እጽ እንደሚጠቀም ብቻ አልነበለም የደረሱበት፤ ሌላም ነገር አለ።

### 2. EPISODE 12, LINES 87 – 91:

> **ሰብለ**: *(…)*በአንጻራዊነት ዳንኤል እና ምህረት ባል እና ሚስት፣ ባል እና ሚስት እየተጫወቱ ነበርና አሁን የመጀመሪያ ልጃቸውን ለመውለድ እየጠበቁ ነው! *(…)* ***91.*** *(…)*ከዚህ በኋላ እናንተ ሶስታችሁ ከቦንጎ አካዳሚ ታግዳችኋል፡፡.

### 3. NARRATOR:

ምህረት ከ ድሀ ቤተሰቦች ነው የተወለደችው። እናም ቦንጎ አካዳሚ ት/ቤት ለመማር የበቃችው የነጻ ትምህርት እድል በማግኘቷ ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ የእርስ በእርስ ጦርነት ከተካሄደበት ከጎረቤት ሀገር ከላቦሪያ የመጣው የቀድሞ የወንድ ጓደኛዋ፣ ዳንኤልም በዚሁ

ትምህርት ቤቱ ውስጥ አዳሪ ተማሪ ነበር፡፡ ዳንኤል ከትምህርት ቤቱ ቢባረርም በትዉልድ ሀገሩ ላቦርያ ያለዉ ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ ወደእዚያ ለመመለስ አልቻለም፤ በእዚያ ላይ አባቱ ቢደዉልላቸዉም ስልኩን አያነሱም። በላቦሪያ ሁኔታው በጣም አሳሳቢ ሆነዋል። እናም ዳንኤል ጓደኛው በለጠን እንዲረዳው ጠይቆት ነበር:

**4. EPISODE 13, LINES 82 – 83:**

ዳንኤል: (…)አባቴን በስልክ እስካገኘው ድረስ የምኖርበት የሆነ ቦታ ያስፈልገኛል፡፡.

በለጠ : ችግር የለም ዳንኤል እዚህ መኖር ትችላለህ፡፡ ግን በጣም መጠንቀቅ አለብን፡፡ ማንም ማወቅ የለበትም፣ እሺ? ችግር ውስጥ መግባት አልፈልግም፡ ፡

**5. NARRATOR:**

ይህ ሁሉ ከተከሰተ እስካሁን ድፍን ሁለት ወራት አለፈዋል፡፡እናም በዚህ መሀል አዳጊዎቹ ወጣቶች ህይወት ዉስጥ ምን እንደተከሰተ እንከታተል…ዛሬ የምናደምጠዉ አስራ አራተኛ ክፍል ድራማ ርዕስ «ራስን መሆን» ይሰኛል። ታሪኩ የሚጀምረዉ ታንዲካ ከተሰኘዉ ጎስቋላ ሰፈር ውስጥ በሚገኘው የእነምህረት ቤት ነዉ፡

## <u>SCENE 1: ምህረት AND ቅዱስ IN TANDIKA</u>

**6. ATMO: TANDIKA, DAYTIME, INTERIOR**

7. ምህረት: (snores lightly)

8. ቅዱስ: (yawns)

9. ቅዱስ: ምህረት፣ ተኝተሻል?

10. ምህረት: (wakes up) አይ፣ ትንሽ ደክሞኝ ነዉ አልተኛሁም። ምንድን ነው የእናቴ ልጅ?

11. ቅዱስ: እማዬ መቼ ነዉ የምትመለሰዉ?

12. ምህረት: እኔንጃ አላውቅም፤ እንደውም ወዴት እንደሄደች እንኳ አልነገረችኝም። ለምን ፈለግሀት?

13. ቅዱስ: እርቦኛል። (realizing) እ እ,,,ምህረት፣ ላለፉት ጥቂት ሳምንታት በየቀኑ ምግብ የምትሰሪልን አንቺ ነበርሽ። ዛሬስ ለምን አትሰሪልንም?

14. ምህረት: (annoyed) ቅዱስ፣ ለምንድን ነው ወጥተህ የማትጫወተው? እኔ ትንሽ ማረፍ እፈልጋለሁ.

15. ቅዱስ: መጫወት አልፈልግም። ብሩክ የሌለበት ጨዋታ ያስጠላል። ምህረት፣ ወንድማችን ይህን ሁሉ ጊዜ ሆስፒታል የቆየው ለምንድን ነው ግን?

16. ምህረት፡ ቅዱስ ምክንያቱን ነገሬሃለሁ፣ እርሱ ታሚል የሳንባ ነቀርሳ የሚባል በሽታ ይዞታል። አንድ ሰው የሳንባ ነቀርሳ ከያዘው ለመዳን ረጅም ጊዜ ይፈጅበታል

***KW BEGIN***

17. ቅዱስ: ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

18. ምህረት: ወደ ስድስት ወራት

19. ቅዱስ: እና እስከ አሁን ምን ያህል ጊዜ ሆነው?

20. ምህረት፡ ሁለት ወር

21. ቅዱስ፡ ታዲያ ከዚያ የበለጠ ጊዜ ይቆያል?

22. ምህረት፡ አይ፣ ቅዱስ፣ እንግዲህ ይህን ጥያቄህን አቁም እባክህን!

***KW*** END

23. ቅዱስ (yawns) ምህረት፣ በጣም እርቦኛል!

24. ምህረት፡ (sighs) ተመልከት፣ እኔም እርቦኛል፣ ግን ቆይ እናታችንን እንጠበቅ፣ እሺ?

25. ቅዱስ፡ አንቺማ ሆድሽ እንደዚህ ተነፍቶ እንዴት ይርብሻል? እየዋሸሽ ነዉ.

**26. ምህረት:** **(embarrassed )** ቅዱስ!

**27. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: ወ/ሮ ሉሊት TALKS TO PRINCIPAL ሰብለ**

**28. ATMO: BONGO ACADEMY EXTERIOR + LIGHT TRAFFIC**

**29. ወ/ሮ ሉሊት :** እባክህ ጥበቃ ርዕሰ መምህርት ሰብለን ለማናገር እንድገባ ፍቀድልኝ። ሴት ልጄ...ማለቴ ...የዚህ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበረች። ረጅም ጊዜ አልቆይም

**30. ጥበቃ:** መጀመሪያ ቀጠሮ ሊኖርሽ ይገባል፤ እመቤት ሰብለ ስራ ይበዛባቸዋል፣ በጣም ስራ ይበዛባቸዋል

**30 a. SFX: VEHICLE APPROACHES AND STOPS, HOOTS**

**31. SFX: ENGINE STILL RUNNING**

**32. ጥበቃ:** ለእመቤት ሰብለ በሩን እየከፈትኩት ስለሆነ ከመግቢያው ዞር በይ.

**33. SFX: GATE OPENED**

**34. SFX: CAR WINDOW ROLLS DOWN**

**35. ሰብለ:** ሁሉም ነገር ሰላም ነው?

36. **ጥበቃ:** ሁሉም ነገር ደህና ነው አትዩ ሰብለ። ምንም ችግር የለም

37. **ወ/ሮ ሉሊት :** **(cuts in)** ይቅርታ፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ፣ ስሜ ሉሊት ይባላል። ምህረት ሙላቱ የእኔ ልጅ ናት። ላናግሮት እችላለሁ? ጥቂት ጊዜ ብቻ ይስጡኝ

38. **ሰብለ:** አሀ የምህረት እናት እርሶ ኖት! ስላገኘሁት ደስ ብሎኛል። አሁን ግን እየወጣሁ ስለሆነ አዝናለሁ። ስለዚህ ነገ እንዲመጡ እጠይቆታለሁ

39. **ወ/ሮ ሉሊት :** እባክዎ-አምስት ደቂቃዎች ብቻ ይስጡኝ

40. **ሰብለ:** **(sighs)** እሺ ይግቡ መኪና ዉስጥ፤ ወደ ከተማ እየሄድኩ ነዉ፣ እየነዳሁ ማዉራት እንችላለን

41. **SFX: CAR DOOR OPENS (HEARD FROM OUTSIDE)**

42. **SFX: FOOTSTEPS ወ/ሮ ሉሊት**

43. **SFX: ወ/ሮ ሉሊት GETS IN CAR**

44. **SFX: CAR DOOR SHUTS (HEARD FROM INSIDE)**

45. **SFX: CAR STARTS TO DRIVE (HEARD FROM INSIDE)**

46. **ATMO: INSIDE MOVING VEHICLE, TRAFFIC OUTSIDE**

**47. ወ/ሮ ሉሊት :** **(struggles to talk)** መምህርት ሰብለ፣ እኔ…እርሶ…ከርዕሰ መምህር ጋር ተነጋግሬ አላውቅም… ግን …ወ/ሮ ሠብለ ፣ ነገሩ ለእርሷ በጣም ከባድ ነው! ምህረት ከተባረች ሁለት ወራት ሆናት፤ ልጄ መብላት መጠጣት፤ መተኛትም አልቻለችም ፡፡ ምንም እንኳ ነፍሰ ጡር ብትሆንም ክብደቷ በጣም ቀንሷል! አባኮ እመቤቴ ! ትልቅ ስህተት ፈጽማለች፣ ግን ከስህተቷ ተምራለች፤

**48. ሰብለ:** የምህረት እናት፣ ብረዳዎ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ግን እግዚአብሔር በሚያውቀዉ ሞክሬአለሁ፡ ህግ መቼም ህግ ነውና ለእከሌ በተለየ የሚባል ነገር የለም፡፡ ለእርሶም ልጅ የተለየ ነገር የለም

**49. ወ/ሮ ሉሊት :** ግን ሊያደርጉት የሚችሉት የሆነ ነገር መኖር አለበት! ልጄ የቤተሰቡ ትልቅ ተስፋ ናት፡፡ ከፍተኛ ትምህርት መማር የቻለች ብቸኛዋ ሰው ናት፡፡ አባኮዎን ርዕሰ መምህርት ሰብለ አንድ እድል ይስጧት

***KW BEGIN***

**50. ሰብለ:** የምህረት እናት አንድ ነገር ልንገርዎ፡፡ ልጅ እያለሁ የእኔም ቤተሰቦች በጣም ድሆችነበሩ፡፡ ልክ እንደ እርሶ ልጅም ለመማር እጓጓ ነበር፡፡ ለእዛም ነው በምህረት ላይ ትልቅ ተስፋ አድርጌ የነበረው፡

**51. ወ/ሮ ሉሊት :** ግን --

**52. ሰብለ:** ቆይ፣ አልጨረስኩም። በተሰጣት እድል ደስተኛ እንደምትሆን ጠብቄ ነበር። እኔም እራሴ በእርሷ ላይ ተስፋ እና ምኞት ነበረኝ። ያንን ደግሞ በግልጽ ነግሬያታለሁ። ግን ልጅዎ አሳፈረችኝ። አሁን ግን ምንም ማድረግ አይቻልም፤ ውጤቱን መቀበል ያለባት ይመስለኛል፡

**53. ወ/ሮ ሉሊት :** **(cuts in)** ግን ወ/ሮ ሰብለ፣ ትምህርት ለሴት ልጅ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ይረዳሉ ብዬ አስባለሁ! እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እኔ እራሴ እንኳ ይህን አልተረዳሁትም ነበር! በትምህርቴ ብዙም አልገፋሁም፤ ጥቂት ዓመታት ብቻ ነው የተማርኩት። ግን አሁን ባለቤቴ ...ሲሄድ፣ በእርሱ ላይ ምን ያህል ጥገኛ እንደነበርኩ ገባኝ፡ ፡ ገንዘብ ያመጣ የነበረው እርሱ ፣ ውሳኔዎቹን ሁሉ ይወስን የነበረውም እሱ ነበር። አሁን ግን ለእህል ውሃ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት የምታገለው እኔው ነኝ። ታዲያ ይህ ልጄ ላይ እንዲደገም አልፈልግም! የመማር ከፍተኛ ፍልጎቱ አላትት። ማጥናት የምትፈልገው ህክምና እንደሆነ በአንድ ወቅት ነግራኛለች!

**54. SILENCE**

**55. ሰብለ:** የምህረት እናት፤ አላስጨረሱኝም እኮ፣

**56. ወ/ሮ ሉሊት :** ይቅርታ። ይቅርታ…እንደው …ለልጄ ሁለተኛ እድል እንዲሰጣት ስለጓጓሁ ነው!

**57. ሰብለ:** ያው እንደነገርኩዎ፤ ምህረት ውጤቱን መጋፈጥ አለባት ነዉ፣ አገዳዉ ደግሞ ጊዜያዊ ነው፣ (sighs)

***KW END*** በዚህ ጉዳይ ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ የምሰጠው እኔ አይደለሁም። የትምህርት ቤቱ የስነ-ስርዓት ቦርድ ነው። በጣም ጎበዝ ልጅ ስለሆነች ትምህርት ቤት ውስጥ እንድትቀር ጥሬአለሁ አሁንም በጣም እየጣርኩ ነው። ግን የመወሰኑ ስልጣን የእኔ አይደለም፣

**58. ወ/ሮ ሉሊት :** (sighs) እሃ ገባኝ፤ ወ/ሮ ሰብለ ጊዜዎን ስለወሰድኩቦዎ እና ስለ ተባበሩኝ አመሰግናለሁ። በእውነት ቀና ሰው ነዎት። እባክዎን እዚህ ጋር ልውረድ? እዚህ ጋ ይጣሉኝ!

**59. SFX: CAR BRAKES AND STOPS, ENGINE STILL RUNNING**

**60. ሰብለ:** ይቻላል። ከመሄዶ በፊት ግን አንድ ነገር ልንገሮዎ፤ ተስፋ አይቁረጡ፣ ምህረትም ተስፋ እንዳትቆርጥ ያበረታቷት። አሁንም የሞያ ስልጠና፣ ወይም ፖሊቴክኒክ የመሳሰሉ ሌሎች ስልጠናዎች

አሉን፡

61. ወ/ሮ ሉሊት : አሁንማወደ ትምህርት ቤት መሄድም አትችልም!የሙያ ስልጠና?

62. ሰብለ: አዎ፤ የሙያ ስልጠና ።

63. ወ/ሮ ሉሊት : ምንድን ነው እሱ?

64. ሰብለ: የሙያ ትምህርት ቤቶች እና ፖሊቴክኒኮች የግድ የቀለም ትምህርት ቤቶች ባይሆኑም ክህሎቶችን ያስተምራሉ። ምህረትም የሆነ ቦታ የምታገኝበት ወይም ለራሷ የምትሰራበት እንደ ልብስ ስፌት፣ የሆቴል ሙያ የመሳሰሉትን መማር ትችል ነበር፡

65. ወ/ሮ ሉሊት : (disappointed) ልጄ የምትፈልገው ያንን አይመስለኝም። ምህረቴ በጣም ጎበዝ ልጅ ናት። መጽሐፍት ማንበብ ነው የምታፈቅረው።፡

66. SFX: DOOR OPENED

67. ሰብለ: እባክዎ እንደ አማራጭ ቢሆንም ያስቡበት። ደህና ይሁኑ የምህረት እናት፡

68. ወ/ሮ ሉሊት : ደህና ይሁኑ

69. SFX: DOOR CLOSED

**70. SFX: CAR DRIVING OFF (heard from outside)**

**71. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: በለጠ AND ዳንኤል FIGHT OVER BLANKET</u>**

**72. ATMO: BONGO ACADEMY, DORMITORY (INTERIOR), EARLY MORNING ATMO**

**73. ዳንኤል:** **(snores heavily)**

**74. SFX: በለጠ TURNING OVER IN BED**

**75. በለጠ :** ስማ ዳኒ!እንዴ ጀለስ! ብርድልብሱን ጠቅልለህ ለራስህ ወሰድከው፣ እኮ!

***KW BEGIN***

**76.** ዳንኤል: **(snores loudly)**

**77. SFX:** ዳንኤል **BEING SHAKEN**

**78. በለጠ :** **(shakes him)** ተው እንጂ ዳንኤል! የተኛህ ለመምሰል አትሞክር፣ እየሰማኸኝ እንደሆነ አውቃለሁ! ዳኒ!

**79.** ዳንኤል: **(wakes up confused)** ምን? እየመጣች ነዉ? ርዕሰ መምህርት ሰብለ…? ነግቷል እንዴ?

80. በለጠ ፡ አዎን፣ ነግቷል። ብርድልብሱን ጠቅልለህ ወሰድከው እኮ። ብርድ ገደለኝ!

***KW END***

81. ዳንኤል: (sleepily) ኦህ…አዝናለሁ፤ ይኸዉ እስክትነሳ ድረስ አብረን እንልበስ

**82. SFX: BLANKET RUSTLES AS THEY SHARE**

***KW BEGIN***

83. በለጠ ፡ (unhappy) እሺ። ግን በናትህ አታንኮራፋብኝ! እንደ እንቁራሪት አጠገቤ ተጋድመህ እያንቋረርክ እኮ መተኛት አልቻልኩልም፣

84. ዳንኤል: ሄ፣ ስማ፣ ማለቴ ፣ይቅርታ ሰማህ! ትንሽ እንተኛ፣ እሺ?

85. በለጠ ፡ (Sarcastic) እሺ ትክክል!

***KW END***

86. በለጠ /ዳንኤል: **BREATHE PEACEFULLY**

**87. SFX: ALARM RINGS**

88. በለጠ ፡ (yawns) *ለሊት* ትንሽ እንኳን መተኛት አልተቻለም። ምን እንደው ልነሳ በቃ፣.

**89. SFX: BED CREAKS AS በለጠ GETS UP**

**90. SFX: ALARM OFF**

**91. SFX: BAREFOOT FOOTSTEPS - በለጠ**

92. ዳንኤል: **(mumbles happily)** ብርድልብሱ ተመልሶ የእኔዉ ሆነ የእኔ…

93. በለጠ : ሄይ፣ ዳንኤል፣ ነጩን ሙታንታዬን አተኸዋል?

94. ዳንኤል: አላ,,,,,የሁም

95. በለጠ : እንዲደርቅ አልጋው ጠርዝ ላይ ያሰጣሁትን ካኒቴራዬን አላየኸ ም?

96. ዳንኤል: **(remembers)** A?! ነጩ የውስጥ …አዎ የለበስኩት መሰለኝ፣

97. በለጠ : የለበስኩት መሰለኝ ምን ማለት ነው?

98. ዳንኤል: እእ፣ ምን መሰለህ በቃ የልብስ እጥረት ገጠመኝ። ደግሞ፣ያው ልብሴ በአጠቃላይ ከነ ሻንጣዬ አየር ማረፊያ እንደሆነ ታውቃለህ። ስለእዚህ ያው ተዋስኩህ ማለት ነዉ ።

99. በለጠ : **(not amused)** ተዋስኩህ?! ሰውዬ፣ ሳትጠይቀኝ እቃዎቼን ሁሉዝም ብለህ መዋስ አትችልም፡፡ ሰውዬ ያ የውስጥ ሱሪዬ ነው። እና ደግሞ የውስጥ ሱሪ በጋራ አይለበስም እሺ! ገባህ?

**100. ዳንኤል:** አዝናለሁ በለጠ !

**101. በለጠ :** (deep breath) ዳንኤል፣ ታውቃለህ? አሁን መሄድ ያለብህ ይመስለኛል፡፡

**102. ዳንኤል:** (surprised) ምን?

**103. በለጠ :** ሰምተኸኛል፡፡ እዚሁ ኪሲምባ ውስጥ ወዳለው አጎትህ ወይም ወደ ሀገርህ፤ መሄጃ ጊዜህ አሁን ይመስለኛል፡

***KW BEGIN***

**104. ዳንኤል:** ተው እንጂ፣ በሌ ፤ እንዲህማ አታመርም፡፡ ጓደኞች «የሆንን» መስሎኝ ነበር።

**105. በለጠ :** ጓደኞችማ ነን፡፡ ለሁለት ወራት ያህል እዚህ እንድትቆይ ያደረግኩህም ለእዚህ ነው፡፡ ግን የሚሆን አይመስለኝም፤ ማለቴ፣ እነዚህ የሚሸቱ ካልሲዎችህን እዚህም እዚያም እያዝረከረክህ፣ በእዛ ላይ ሌሊቱን ሙሉ እያንኮራፋህ እኔ መተኛት አልቻልኩም፡፡ ከዚህ በላይ እዚህ አንተን ደብቆ ማስቀመጡ ደግሞ ከባድ ጭንቅ ውስጥ መግባት እንደሆነ መንገሩ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡.

***KW END***

106. ዳንኤል፡ ይህ ሁሉ በእዛ ተራ የውስጥ ሱሪ ምክንያት መሆኑ ነው?

107. በለጠ ፡ ያ ተራ የውስጥ ሱሪ ቢሆን የእኔ የግሌ የውስጥ ሱሪ ነው! እናም ሳትጠይቀኝ የውስጥ ሱሪዬን መውሰድ የለብህም! ያ መዋስ ሳይሆን ሌብነት ነው!

108. ዳንኤል፡ አሀ፣ እንዴ፣ ተው እንጂ ጆለስ...

109. በለጠ ፡ አይሆንም። ሂድ በቃ አሁን ዳኒ፣እንደውም እነዚያን የውስጥ ሱሪዎች ስለማልፈልጋቸው አንተ ጋር ሊቆዩ ይችላሉ !

110. ዳንኤል፡ (sighs)

**111. OUTRO – NARRATOR:**

ለዛሬ እስከዚሁ ነበር። ዳንኤል፣ የት ይገባ ይሆን? በመጨረሻ አባቱን ላቦሪያ ውስጥ በስልክ ማግኘት ይችል ይሆን? ምህረትስ? ትምህርቷን እንድትቀጥል እናቷ መታገላቸዉን መቀጠሉ ይሳካላቸዉ ይሆን? የእነዚህን መልሶች በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ ይከታተሉ። ያለፉትን ክፍሎች ማድመጥ ከፈለጋችሁ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኛሉ። በፌስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ እስክንገናኝ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።